# የኢህአዴግ "አብዮታዊ ዲሞክራሲና" ችግሮቹ

## ከመረራ ጉዲና (ዶ/ር)

## ለምምክክር መድረክ በኢትዮጵያ ለውይይት መነሻነት የቀረበ ጽሑፍ

## ታህሳስ 18 /2001 ዓ.ም

## I. መግቢያ

ላለፉት 18 ዓመታት አካባቢ ኢህአዴግና መንግሥቱ "አብዩታዊ ዴምከራሲ" በሚለው ፍልሰፍና አየተማሩ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትንና የዴሞክራሲ ተቋማትን በሚያመረቃ ሁኔታ እየገነቡ እንደሚገኙ ያለመሰልቸት ሲነግሩን ኖረዋል። በዚሁ "አብዩታዊ ደምክራሲ" በተባለው የፓለቲካ ፍልስፍና ላይ በመመሥረትም የኢትዮጵያ ብሔሮችና ብሔረሰቦችን እኩልነት ያረጋገጠው የፌዴራል ሥርዓትንም መገንባት መቻላቸውንም ሲያስገነዝቡን ኖረዋል። በዚሁ ውጤታማ ፍልስፍናዩ ነው በሚለው በመመራትም አስተማማኝ የሆነ ሰላምና መረጋጋትን፣ ድንቅ የሆነ ፈጣን ልማት ለሃገሪቷና ለሕዝቦችዋ ማምጣት መቻላቸውን እየሰበኩ ነው። በዚሁ ተአምራዊ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገትም ሀገራችንን በሁለት አሥርተ ዓመታት መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ እንደሚያደርሷትም የኢህአዴግ መሪዎች በሙሉ ልብ ሊያሰሙን እየሞከሩ ነው።

ነገር ግን ፣የኢትዮጵያ ምሁራን ብቻ ሳይሆኑ ስለኢትዮጵያ መጠነኛ ዕውቀት ያላቸው የውጭ ምሁራንም አብዛኛዎቹ ስለ ኢህአዴግ "አብዩታዊ ዴሞክራሲ" ዴሞክራሲያዊነትም ሆነ ስለተገኘው ድንቅ ድል ማመን አልቻሉም። እንደውም፣ የኢህአዴግ "አብዮታዊ ዴምክራሲ" በከፍተኛ ችግሮች የተተበተበ መሆኑን በበቂ ማስረጃዎች እያረጋገጡ ናቸው። እንደአያያዛችን በሁለት አሥርተ ዓመታት መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለመድረስ መቻሉም ከኢህአዴግ ሕልም የዘለለ ያለመሆኑንም ያሰምሩበታል።

በአፄዎች ዘመን ጀምሮ በባዶ ተስፋ ሲታለል የኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብም ፣ ቃልና ተግባራቸው ሁሌም ለየቅል በሆነው የኢህአዴግ መሪዎች ዲስኮር የሚማልል ልብ ያለው አይመስልም። በሌላ አባባል፣ በዛሬው የኢትዮጵያችን ሁኔታ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሚያምኑት እግዚአብሔር እንኳ ኢህአዴግንና መንግሥቱን እመኑ ፣ ሰላምና ብልጽግና እየመጣላችሁ ነው ፣ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እየተገነባላችሁ ቢል ብዙ አማኝ የሚገኝ አይመስልም። ዋናው ጥያቄ ሕዝብና መንግሥት የማይተማመኑበት ሁኔታ የፈጠሩት "አብዩታዊ ዴሞክራሲና የአብዮታዊ ዲሞክራቶች" መንግሥት ባህሪያት ምንድናቸው? የሚለው ጥያቄ ነው።

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ፣ በአንድ በኩል የኢህአዴግ "አብዩታዊ ዴሞክራሲ" ከዓለም አቀፍ የዴሞክራሲ ፍልስፍና ተመክሮ አንፃር ማየትና በሌላ በኩል ደግሞ ይህ በችግሮች የተተበተበ ፍልስፍና ሀገሪቷንና

ሕዝቦቿን ወዴት እየመራ እንደሆነ ለማሳየት ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት በኢትዮጵያችን ሁኔታ አማራጭ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታን መንገዶችንም ለመጠቆም ነው፡፡

## II. የዴሞክራሲ ፍልስፍና ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮዎች

በዛሬዋ ዓለም ከሞላ ጐደል ሰፊ ተቀባይነት ያገኘው የዴሞክራሲ ትርጉም የአብርሃም ሊከኑ "የሕዝብ መንግሥት ፣ በሕዝብ ለሕዝብ" የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ እዚህ ላይ ልብ ማድረግ የሚያስፈልገው ትልቁ ቁም ነገር ፣ በግሪኮች ዘመን የነበረው ቀጥተኛ ዴሞክራሲም /Direct Democracy/ ሆነ በዛሬዋ ዓለም እየተገበረ ያለው የውክልና ዴምክራሲ /Representative Democracy/ በሕዝብ ተሳትፎ ለሕዝብ የሚያገለግል መንግሥት የመፍጠሩ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ማለት ፣ሌሎች ሕዝቡን ተክቶ የሚፈጥሩት ሳይሆን ሕዝቡ በራሱ ለራሱ የሚመሠርተው መንግሥት መሆኑን ነው፡፡

ሌላው ልብ ማድረግ የሚያስፈልገው ጉዳይ በዴሞክራሲ ላይ ሰፊ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ለሕዝቡ አገልግሎት በሕዝቡ መፈጠር ላለበት መንግሥት የየራሳቸው ትርጉም ቢሰጡም መከተል ባለባቸው መሠረታዊ መመዘኛዎች ተመሳሳይነት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

**ለምሳሌ፣** ሊፒሴት የተሰኘ ታዋቂ ስለዴሞክራሲ ያጠና ምሁር ፣ ዴምክራሲን ሲተረጉም በጊዜ የተወሰነ ፣ መሪዎችን ለመለወጥ የሚያስችል ሕጋዊ ዕድል የሚሰጥ የፖለቲካ ሥርዓት የሆነ ፣ አብዛኛው ሕዝብ በወሳኝ ውሳኔዎች አሰጣጥ ላይ በቂ ተፅእኖ ለማድረግ እንዲችል ፣ ለፖለቲካ ሥልጣን ተወዳዳሪዎችን ለመምረጥ የሚፈቅድ ሥርዓት ነው ይላል፡፡ ፒኖክ የሚባል ሌላው የዴሞክራሲ ምሁር ደግሞ ፣ ዴሞክራሲ የመንግሥት ፖሊሲዎች በቀጥታም በመራጮች ድምጽ ወይም በተዘዋዋሪ በነፃና በጊዜ በተገደበ ምርጫ በሕዝብ የተመረጡ ተወካዮች የሚወስኑበት ሥርዓት ነው ይለናል፡፡[1]

አሁንም ሌላኛው ቫንሃን የሚባል የዴምክራሲ ምሁር የተለያዩ ቡድኖች በሕግ በተደነገገው መንገድ ለመንግሥት ሥልጣን የሚወዳደሩት ባለሥልጣናት በሕዝብ የሚመረጡበትና ለሕዝብ ተጠያቂ የሚሆኑበት ሥርዓት ነው ብሎ ያስቀምጣል፡፡
በተለይ በዴምክራሲ ላይ ባደረጋቸው ሰፊ ጥናቶች በደምክራሲ ጠባብትነት የሚታወቀው ደሐል ዴሞክራሲን ከብዙሀን አገዛዝ /Polyarchy/ ጋር አንድ ከማድረጉ በላይ ሁለቱም የሚከተሉትን ሶስት መሠረታዊ ጉዳዮችን የሚያሟሉ መንግሥታትን ይወክላሉ ይላል፡፡

**እነሱም ፣**

1ኛ. ትርጉም ያለው ፣ በግለሰቦችና በተደራጁ ቡድኖች መካከል ለሁሉም የመንግሥት

[1] ሁሉም በእንግዚለኛ ከተጻፉ ጽሑፎች የተወሰዱት ትርጉማቸው የኔ ናቸው፡፡

ሥልጣን እርከኖች ሰፊ ውድድር የሚፈቅድ፣ በጊዜ የተገደበ ሥልጣን ላይ የተመሠረተና ኃይልን የማይጨምር የሥልጣን ውድድር ያለበት፣

2ኛ. በጣም አሳታፊ በሆነ መንገድ መሪዎች እንዲመረጡ ዕድል የሚሰጥና ፍትሐዊ ምርጫ ላይ የተመሠረተ፣

3ኛ. የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ያሰፈነ ማለትም ፣ የመናገር መብት ፣ የመጽሐፍ መብት ፣ የመደራጀት መብትና አሳማኝ የፓለቲካ ተሳትፎ የሚያሰፍን ናቸው ይላል።

ደሐል የፓለቲካ ሥርዓት ክፍት መሆኑን ፣ የፓለቲካ ተሳትፎንና ፍትሐዊ ምርጫን ያስምርባቸዋል። እዚህ ላይ ከሁሉም በላይ ልብ ማድረግ የሚያስፈልገው ፣ የአራቱንም ምሁራንን አስተሳሰቦች የሚያገናኘው መሠረታዊ ጉዳይና ዴምክራሲ መሪዎች በሕዝብ ነፃ ምርጫ የሚሰየሙበት የፓለቲካ ሥርዓት መሆኑን ነው። ይህም የሚያሳየው ነፃ ምርጫ ለአንድ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መኖር የመጨረሻ (Minimal) ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ነው።

ከዚህም አልፎ አሁን ካሉት የዓለም የዴምክራሲ ሥርዓት ተሞክሮዎች በመነሳት ሁብር ፣ ሩሼሜዬርና ስትፌን የሚባሉ የዴሞክራሲ ጠባብት ሶስት የዴምክራሲ ሞዴሎችን ለይተው ያስቀምጣሉ።

**እነዚህም፣**

1ኛ. ፎርማል ዴሞክራሲ (Formal Democracy)

2ኛ. አሳታፊ ዴሞክራሲ (Participatory Democracy)

3ኛ. ሶሻል ዴሞክራሲ (Social Democracy) ናቸው።

በነሱ እይታ ፣ ፎርማል ዴሞክራሲ የሚያካትታቸው መሠረታዊ ጉዳዮች በየጊዜው የሚካሄዱ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ፣ የሁሉም ዜጐች የመምረጥ መብት ፣ መንግሥታዊ ተቋማት ተጠያቂነታቸው ለሕዝብ እንደራሴዎች የሆነበት፣ ለመናገርና ለመደራጀት መብቶች ዋስትና የሚሰጥና በዘፈቀደ የመንግሥት አካላት እርምጃ የሚከለክል የፓለቲካ ሥርዓት ነው። በእነሱ አመለካከት እንዲህ ዓይነቱ የፓለቲካ ሥርዓት እኩል የፖለቲካ ሥልጣን አከፋፈል የሌለውና የማህበራዊና የኢኮኖሚ እኩልነት አያሰፍንም።

እነሱ እንደሚሉት የፎርማል ዴሞክራሲንና እኩል የፓለቲካ ክፍፍልን የሚጨምረው አሳታፊ ዴሞክራሲ የተሰኘው ነው።

የፎርማል ዴሞክራሲ መስፈርቶችን፣ የአሳታፊ ዴሞክራሲ መስፈርቶችንና ማህበራዊና የኢኮኖሚ እኩልነት የሚያካትተው ደግሞ ሶሻል ዴሞክራሲ የተሰኘ ይሆናል።

ዴሞክራሲ በዳበረባቸው ምዕራባዊ ዓለም ፣በጃፓን ፣ በሕንድ ፣ በደቡብ ኮሪያ በመሳሰሉት ሀገሮች ስፋት ያለው ዴሞክራሲ ከሶስቱ ሞዴሎች አንዱ ነው፡፡ በአንዳንዶቹ ግራ ዘመም ፓርቲዎች ሲያሸንፉ፣ የሶሻል ዴሞክራሲ አስተዳደር የሚፈጠርበት ፣ ቀኝ ዘመም ፓርቲዎች ሲያሸንፉ ደግሞ ፎርማል ዴሞክራሲ የሚፈጠርበት ሁኔታዎች ይኖራሉ፡፡

**ለምሳሌ፣**

የእንግሊዝ ሌበር ፓርቲን ጨምሮ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲዎች በጀርመን ፣ በፈረንሳይ ፣ በኔዘርላንድና በአብዛኛው የእስካንዴቪያን ሀገሮች ሥልጣን ሲይዙ ኖረዋል፡፡ በተለይ ቀኝ ዘመም ፓርቲዎች በእንግሊዝ ፣ በፈረንሳይ ፣ በጀርመን ሥልጣን ይዟል፡፡ ዛሬ በፈረንሳይና በጀርመን ሥልጣን ላይ ያሉት ቀኝ ዘመም ፓርቲዎች ሲሆኑ ፣ በእንግሊዝ ግራ ዘመም ሌበር ፖርቲ ነው፡፡ በአሜሪካ መሠረታዊ ልዩነት ብዙ ጊዜ ባይታይባቸውም በቀኝ ዘመምነት የሚታወቀው ሪፑብሊካን ፖርቲ ሲሆን፣ በግራ ዘመምነት የሚታወቀው ደግም የዴሞክራቲኩ ፓርቲ ነው፡፡

እዚህ ላይ ልብ ማድረግ የሚያስፈልገው ፣ ቀኝ ዘመም ፓርቲምች መንግሥት በኢኮኖሚ ጉዳዮች ጣልቃ እንዳይገባ የሚከለክሉና ሀብትን ማደላደል የነፃ ገበያ ሥርዓት ጉዳይ ነው ብሎ ሲያምኑ ፣ ግራ ዘመም ፓርቲዎች ደግሞ መንግሥት ሀብትን ለማደላደልና ትምህርት ፣ ሕክምና ወዘተ የመሳሰሉትን ለዜጎች ለማዳረስ ኢኮኖሚ ውስጥ ጣልቃ መግባትን የሚደግፉ ናቸው፡፡

ዴሞክራሲ ከዳበረባቸው ሀገሮች ተሞክሮ ተነስቶ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ስለሚያደርጉ ሀገሮች ያጠኑ የፓለቲካ ጠበብት ደግም ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር ወሳኙ የመሸጋገሪያ ድልድይ ነፃ ምርጫ መሆኑን ከማስቀመጣቸውም በላይ ፣ ለምርጫው ፍትሐዊነት ማረጋገጫ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን በማይሻማ ቋንቋ ያስቀምጣሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ብራቴንና ቫንዲቫል የሚባሉ የአሜሪካ ፓለቲካ ሳይንቲስቶች ስለዴሞክራሲያዊ ሽግግር በሚመለከተው መጽሐፋቸው ውስጥ (ኢትዮጵያም ደረጃው እዚህ ነው) የሚከተሉትን ያስገነዝባሉ፡፡

> ምርጫ የሲቪል መብቶች በተከበሩበት ሁኔታ መካሄድ አለበት፡፡ የሲቪል መብቶች መኖር በተግባር በሐቅ ምርጫ እንዳለ ዋስትና ይሰጣሉ፡፡ ከምርጫው በፊት ሁሉም ለመወዳደር የሚፈልጉ ተወዳዳሪዎች ራሳቸውን ለሥልጣን የማጨት ዕድል እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ የራሳቸውን የፓለቲካል አስተሳሰብ በግልጽ መናገር መቻል አለባቸው፡፡ ድጋፍ ለማሰባሰብ የፈለጉትን የፓለቲካ ድርጅት መፍጠር መቻል አለባቸው፡፡ በዚሁ አኳያ ዜጎችም የፈለጉትን የፓለቲካ መረጃ በነፃ የማግኘት መብት መጠበቅ አለበት፡፡ የፈለጉትን የፓለቲካ ድርጅት ውስጥ የመሳተፍ መብታቸውም የተጠበቀ መሆን አለበት፡፡[2]

[2] ሁሉም በእንግዚለኛ ከተጻፉ ጽሑፎች የተወሰዱት ትርጉማቸው የኔ ናቸው፡፡

በአፍሪካ ተሞክሮ ላይ ተመሳሳይ ጥናት ያካሄደው ዲያሞንድ ፣ በነፃነት ቤት (Freedom House) በተባለው ተቋም ምደባ ላይ በመመርኮዝ የአፍሪካን መንግሥታትን አራት ቦታ ላይ ይመድባቸዋል።

እነሱም፣

1ኛ. ሊበራል ዴምክራሲ (Liberal Democracy)

2ኛ. የምርጫ ዴሞክራሲ (Electoral Democracy)

3ኛ. የይስሙላ ዴምክራሲ (Pseudo Democracy)

4ኛ. አምባገነናዊ አገዛዞች (Authoritarian Regimes) ናቸው።

እኚህ የዴሞክራሲ ምሁር ኢትዮጵያችንን የመደቡት በይስሙላ ዴሞክራሲ (Pseudo Democracy) ምድብ ውስጥ ሲሆን ፣ በዚህ ምድብ ውስጥ የሚገኙ ሀገሮች ባህሪያትም ፣ ዓለም አቀፍ ደረጃን ያልጠበቁ የመድብሉ ፓርቲ ምርጫዎችን ለስሙ የሚያካሄዱ እንደሆኑም ያብራራል። የነዚህ ዓይነቶች ምርጫዎች ሚናም በአንድ በኩል አምባገነን የሆኑ ገዥ ፓርቲዎችን ሥልጣን ላይ እንዲቆዩ ለማመቻቸት ሲሆን ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዞች በሕዝባቸው ፊት በተለይም በዓለም አቀፍ ማህበረሰቦች ፊት ተቀባይነት እንዲያገኙና የተሻለም ገጽታ እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚደረጉ ጨዋታዎች ናቸው። በተለይ ለአንድ ፓርቲ መንግሥታት ሁኔታዎችን ሲያመቻች የነበረው የሶሻሊስት ሥርዓት ከሞላ ጐደል ጡረታ ከወጣ በኋላ በዛሬዋ ዓለም እንዲህ ዓይነቱ ጨዋታዎች እርዳታ ለማግኘት ጭምር ይፈለጋሉ።

ከሁለት ዓመት በፊት የወጣ አንድ የስብስብ ሥራ የሆነ መጽሐፍ የቀዝቃዛ ጦርነቱ ካበቃ በኋላ በምርጫዎች ስም የሚደረጉ ጨዋታዎችን በስፋት የሚያትት አለ። ኢትዮጵያችንም የተጠቀሰችበት ይህ መጽሐፍ በምርጫ ላይ የተመሠረተ አምባገነናዊ ሥርዓት (Electoral Authoritarianism) የተሰኘ ሲሆን ፣ በምርጫ ዙሪያ ያሉትን ግልጽና ሥውር ጨዋታዎችን በጥልቀት የሚመረምር ስብስብ ሥራ ነው። ይህ ስብስብ ሥራ ከሚያነሳው ጉዳዮች አንፃር ኢትዮጵያችንን የሚመለከቱትን ልብ ማድረግ ይጠቅማል።

ይህ ሰብስብ ሥራ (ኢትዮጵያችንም አለችበት) በምርጫ ስም ሥልጣን ላይ የሙጥኝ ብሎ የሚኖሩ አምባገነን ሥርዓቶችን በሦስት ደረጃ ይመድባቸዋል።

እነሱም፣

1ኛ. ጉዶሎ ዴሞክራሲያዎች (Defective Democracies)

2ኛ. የተዳቀሉ አገዛዞች (Hybrid Regimes)

3ኛ. አዲሱ የአምባገነን ሥርዓት (New Authoritarianism) ናቸው

ሁሉም የነፃነት ቤት (Freedom House) የተባለው ተቋም የሚያስቀምጣቸውን ዓለም አቀፍ የነፃና ፍትሐዊ ምርጫ መመዘኛዎችን አያማሉም።

***መመዘኛዎቹም፣***

*1ኛ. ዋናው የሥራ አፈጻሚና ሕግ አውጪው /ፓርላማው/ በነፃና ፍትሐዊ ምርጫ መመረጡ፣*

*2ኛ. የዜጐች ያለምንም ተፅእኖ የመደራጀት መብት መኖር፣*

*3ኛ. ፍትሐዊ የሆኑ የምርጫ ሕጐች መኖር፣*

*4ኛ. ፓለቲካ ፖርቲዎች እኩል የመንቀሳቀስ መብት መኖር፣*

*5ኛ. መራጩ ሕዝብ በነፃነት ድምጽ የመስጠትና ድምጹም በሐቅ የመቆጠር ሁኔታ መኖር፣*

*6ኛ. የምርጫ ውጤቶች ተወዳዳሪ የፓለቲካ ፖርቲዎች የማሸነፍ ወይም የመውረድ ሁኔታን ማስከተል መቻል፣*

*7ኛ. ተቃዋሚዎች በምርጫ ሥልጣን የመያዝ ዕድል መኖር ናቸው::*

*ከነዚህ መመዘኛዎችና ከዓለም አቀፉ የዴሞክራሲ ተሞክሮዎች ስንነሳ ዴሞክራሲ ከነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ውጭ የማይታሰብ ክስተት መሆኑ ነው::*

*ከላይ ካየናቸው መነሻዎች ተነስተን የኢህአዴግን "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" ስንገመግም ቀጥሎ እንደምናሳየው ዝርያው ከየት እንደሆነ በቀላሉ ማየት ይቻላል::*

## III. የኢህአዴግ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" በተግባር ሲፈተሽ

*በ 1983 ዓ.ም መንግሥታዊ ሥልጣንን በኢትዮጵያ ውስጥ በኃይል ጨብጦ መሠረታዊ ለውጥን በሀገሪቷ በማምጣት፣ የሁሉም ሕዝቦቿ እኩልነት የሚከበርበት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እየገነባሁ ነው ብሎ የሚገዛት ድርጅት ሀገሪቷን ለሁለት አሥርተ ዓመታት ለሚጠጋ ጊዜ እየገዛት ነው:: "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" የተባለው የዚህ ድርጅት ፍልስፍናም ዝቅ ብለን እንደምናየው ቲኦሪና ተግባሮቹ በችግሮች የተተበተቡ በመሆናቸው በእውን የሚታይ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ መፍጠር እንዳልቻለ አከራካሪ ጉዳይ አይደለም::*

*ፋይዳውም ፣ አንድን አምባገነናዊ ፓርቲና መንግሥትን ሥልጣን ላይ ለማቆየት ብቻ እንደሆነ በቂ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል:: በተለይ በኢትዮጵያ ሕዝቦች ሕይወት ውስጥ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት እንዳልቻለ በገሃዱ ዓለም የሚታይ እውነታ ነው:: እንደውም ተጨበጭ ለውጥ ለማምጣት ከመጣር ይልቅ በባዶ ፕሮፖጋንዳ ከመጠመድ አልፎ ፣ የሕዝቦችን ሕይወት ውጤት አልባ በሆኑ ፖሊሲዎች እያመሰቃቀለ ይገኛል:: የዚህ ጽሑፍ ዓላማ እላይ እንዳስቀመጥነው ቃልና ተግባሮቹ ሁሌም የሚጋጩበት ኢህአዴግ የአብዮታዊ ዴሞክራሲውን ፍልስፍና ከየት ተዋሰው? ለምንስ መሣሪያነት እየተጠቀመ ነው? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ከዓለም አቀፍ ተመክሮ በመነሳት ለመመለስ ነው::*

የኢህአዴግ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" ከየት መጣ? የሶሻሊዝም ፅንሰ-ሀሳብ በቀደምት የሶሻሊስት ፈላስፎች፣ እነካርልማርክስ ሲቀመር ፣ የሶሻሊስት አብዮት ይመጣል ተብሎ የተገመተው የካፒታሊስቱ ሥርዓት በዳበረባቸው የምዕራቡ ዓለም ነበር:: ነገር ግን የመጀመሪያውን የሶሻሊስት አብዮት የመሩት እነሌኒን አብዩታዊ ኃይሎች ከተጠናከሩና አርሶ አደሩን ማንቀሳቀስ ከቻሉ ካፒታሊዝም ባልዳበረባቸው ሀገሮችም ቢሆን ወደ ሶሻሊስት አብዮት የሚያደርስ መሸጋገሪያ ድልድይ በመሥራት የተሳካ የሶሻሊስት አብዮትን ማካሄድ ይቻላል የሚል ትንታኔ አቀረቡ:: በዚህም ስትራቴጂ በመመራት እ.ኤ.አ. 1917 ፣ ነፍሷን ይማርና የሶቪየት ህብረትን የፈጠረውን የጥቅምት አብዮትን አካሄዱ::
ከነሌኒን በተሻለና በግልጽ ቋንቋ ፣ሊቀመንበር ማኦ አዲሱ ዴሞክራሲ በተሰኘ ጹሑፋቸው እንዴት ካፒታሊዝም ባልዳበረባቸው እንደ ቻይና በመሳሰሉት ሀገሮች የሶሻሊስት አብዮትን ማካሄድ እንደሚቻል በዝርዝር አስረዱ:: በዚህም ቀመራቸው እ.ኤ.አ. የ1949ን የቻይና አብዮትን በተሳካ ሁኔታ አካሄዱ:: ዛሬ የምናውቃት ቻይናም የዚሁ አብዮት ውጤት ናት::

ይህ የማኦ የአዲሱ ዴሞክራሲ አስተሳሰብም በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄና ከተማሪዎች ንቅናቄም በተወለዱት የፖለቲካ ድርጅቶች በኩል ወደ ሀገራችንም መምጣቱ አከራካሪ ጉዳይ አይደለም:: በጊዜው ወደ ማኦው አዲሱ ዴሞክራሲ ከተሳቡት ውስጥ ከመሐል ሀገር መኢሶንና ኢህአፓ ፣በዳር አካባቢ ከሚንቀሳቀሱት የኤርትራ ሕዝባዊ ነፃ አውጭ ግንባር (EPLF) ይገኙበታል:: ኋላ ኢህአዴግን የፈጠረው ሕወሐትም (TPLF) በዚሁ የሊቀመንበር ማኦ ፍልስፍና ተኮትኩቶ እንዳደገ አጠያያቂ አይደለም::

እዚህ ላይ በውል መገንዘብ የሚያስፈልገው ትልቁ ቁምነገር ፣ የዚህ ፍልስፍና መነሻውም ሆነ መድረሻው የሶሻሊስት አብዮት ለመምጣት እንጂ "ነጭም ሆነ ጥቁር ካፒታሊዝምን" ለመገንባት በፍጹም እንዳልነበረ በዛ ትውልድ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ለነበራቸው ለክርክር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም:: ኢህአዴግ የተላበሰው ይህንኑን ለመሆኑ ድርቅና ካልሆነ በስተቀር የሚያከራክር አይመስለንም:: እንደውም፣ አሁን እንደቀልድ እየተረሳ መጣ እንጂ ኢህአዴግ የምኒሊክ ቤተ መንግሥት እስከገባ ድረስ መሪዎቹ ጫካ ሆኖ በማያሻማ ቋንቋ ሲያስተጋቡ የነበረው ይህንኑን የነማኦን ያልተከለሰና ያልተበረዘ አዲሱን ዴሞክራሲ ነበር:: ሊገነባ የነበረውም ዛሬ እንደሚባለው "ነጭ ካፒታሊዝም" ሳይሆን የሶሻሊስት ሥርዓትን ነበር::

የዛሬውን አያደርገውና ኢህአዴግ በደርግ ዘመን ከነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የነበረው ክርክር ፣ ማን የበለጠ ሐቀኛ ግራ ነው? እንደነበረም የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው:: ከዚህም አልፎ ኢህአዴግ በጊዜው ከነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ሶቪየት ህብረትን እንደሶሻል እምፔሪያሊስት አላያችሁም ብሎ ፀረ ደርግ ኀብረቶችን ሲያፈርስ እንደነበረም ይታወቃል::

እዚህ ላይ ዋናው ክርክር ኢህአዴግ ሶሻሊስት ነው ፣ አይደለም ሳይሆን የሁለቱ ዓለም ዲቃላ የሆነው አስተሳሰብ ለምን ተፈለገ? የዚህ ዲቃላ አስተሳሰብ መዘዞች ለሀገሪቷና ህዝቦቿ ምን እያመጡ

ነው የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ኢህአዴግ ተለውጫለሁ ካለና የመድበሉ-ፓርቲ (Multi-Party) ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እገነባለሁ ካለ፣ በተግባር ወደዚህ በፍጹም በማያመራው "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" ጋር አልላቀቅ ያለው ልዩ ፍቅሩ ምንድ ነው የሚለውን ነጥብ መገንዘብ እጅግ በጣም መሠረታዊ ጉዳይና የኢህአዴግ ፍቅር ሃይማኖታዊ ወይስ ሌላ መሆኑን በውል ለመረዳት ያስችላል፡፡

የመንግሥት ሥልጣንን ጨምድዶ ለመያዝና ከመንግሥት ሥልጣን የሚመነጩትን ጥቅሞች ብቻ ዓለማዎቹ አድርጐ ለሚንቀሳቀስ ኃይል "ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ" አስተሳሰብና አሠራር የተቆራኙ የመሪ ድርጅትና የዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ፅንሰ ሀሳቦች እጅግ በጣም ጠቃሚ መሣሪያዎች ናቸው፡፡

የመሪ ድርጅት ፅንሰ ሃሳብ በተግባር ሲገለጽ ፣ ለአንድ ገዥ ፓርቲ የመሪነት ሚና የሚሰጥና ይህም የመሪነት ሚና የተሰጠው ፓርቲ በህብረተሰቡ ላይ ሁለንተናዊ ቁጥጥር እንዲኖሩት ይፈቅዳል፡፡ ከገዥው ፓርቲ ውጭ ያሉ ፓርቲዎች የሚሰጣቸው የይምሰል ሚና ወይም የአገርነት ሚናን እንጂ ጠንካራ ፓርቲ ሆኖ በመውጣት ሥልጣን እንዲይዙ አይፈቅድላቸውም፡፡ በግልጽ ቋንቋ ለማስቀመጥ ፣ ሚናቸው የገዥው ፓርቲ አገልጋይ መሆን እንጂ ተቀናቃኝ መሆን አይደለም፡፡ የገዥው ፓርቲ መሣሪያ ሆኖ ጨዋታዎቹን የሚያሳምሩለት ወይም ውበት የሚይለብሱት አሻንጉሊቶች እንጂ፣ የራሳቸው ሕልውና ያላቸውና ነገ ገዥ ፓርቲ ለመሆን የሚያስቡ ድርጅቶች መሆን የለባቸውም፡፡

ሌላው ልብ ማድረግ የሚያስፈልገው ጉዳይ ፣ "በአብዮታዊ ዴሞክራሲ" አስተሳሰብ የአንድ ፓርቲ የበላይነትን ለማስፈን መንቀሳቀስ ኃጢያትም፣ ነውርነትም የለውም፡፡ "የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ" በፓርቲና መንግሥት መካከል ፍጹማዊ አንድነትንም ይፈቅዳል፡፡ "በአብዮታዊ ዴሞክራሲ" አስተሳሰብ ልዩ ልዩ የመንግሥት ተቋማትም የገዥው ፓርቲ ጉዳይ አስፈጻሚ መሆን አለባቸው፡፡ "በአብዮታዊ ዴሞክራሲ" አስተሳሰብ ሁሉም የመንግሥት ተቋማትና ሠራተኞቻቸው የገዥውን ፓርቲ ፍጹማዊ አመራር መቀበል አለባቸው፡፡ ይህም ማለት ፣ለሲቪል ሰርቪስ የተቀጠሩ ሠራተኞች በዴሞክራሲያዊ ስርዓት በዳበረባቸው ሀገሮች እንደሚደረገው ከፖለቲካ ፓርቲዎች ፋክክር ነፃ መሆን አይችሉም፡፡ እንደዛም በመሆኑ "አብዮታዊ ዴሞክራሲው" ለታማኝነት እንጂ ፣ለዕውቀትና ችሎታ ብዙውም የማይጨነቅ የካድሬዎች አስተዳደር ይሆናል፡፡

ከሁሉም በላይ "በአብዮታዊ ዴሞክራሲ" አስተሳሰብ ፍ/ቤቶችን ጨምሮ ነፃ የመንግሥት ተቋማት እንዲጠናከሩ ስለማይፈልግ ፣የዘመናዊ የውክልና ዴሞክራሲ መሠረተ ድንጋይ የሆኑትን የሥልጣን ክፍፍል (Separation of Powers) እና አንዱ የሌላውን ሥልጣን መቆጣጠር (Check and Balances) አይኖሩም፡፡ "በአብዮታዊ ዴሞክራሲ" አስተሳሰብ ፣ ነፃ የሲቪል ማህበራትም እንዲያብቡ አይፈቀድም፡፡ "በአብዮታዊ ዴሞክራሲ" አስተሳሰብ፣ ነፃው ፕሬስ የአድሃሪ ኃይሎች መሣሪያ ስለሚሆን ቢታፈን ኃጢያትነት የለውም፡፡

ሌላው "ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ" ጋር የተቆራኘው ችግር፣ ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትና ከዚሁ የሚመነጨው የድርጅት ሥራ የሚባለው ነው፡፡ ከላይ ወደታች በሚለው በዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት አሠራር፣ የመንግሥት ተቋማትም ሆኑ የፓርቲው የበታች አካላት ከፓርቲው ቁንጮዎች ከላይ ወደታች የሚተላለፉ ውሳኔዎችን የሚያስፈጽሙ ዴሞክራሲ አልባ ፍጡራን ይሆናሉ፡፡ በጥቅሉ "አብዩታዊ ዴሞክራሲ" የአንድ ፓርቲ የበላይነትን (One – Party hegemony ) ለመፍጠርና አምባገነናዊ የፓለቲካ ሥርዓትን ለመገንባት በሃያኛው ክፍለ ዘመን የተፈተነ የፓለቲካ ፍልስፍና መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡

የኢህአዴግ "የአብዮታዊ ዴሞክራሲ" ፍቅር የሚመነጨው እላይ ባነሳናቸው ነጥቦች ምክንያት ነው፡፡ ለዚህ ነው ኢህአዴግ የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲን (Multi-party Democracy) በቃል እየሰበከ፣ በተግባር ግን እሱን ሊያወርዱ የሚችሉ ጠንካራ ፓለቲካ ፓርቲዎች እንዳይፈጠሩ ሌት ተቀን ሲኳትን የሚገኘው፡፡ ነፃ የሲቪል ማህበራት እንዲያብቡ እያወጀ፣ በተግባር ግን እንዲሽመደመዱ የሚያደርገው፡፡ ነፃ ገበያ እያለ፣ እዛው በዛው ነፃ ገበያን የሚያዛቡ ራሱ የሚቆጣጠራቸውን የንግድ እምፓዬር (Business Empire) ፈጥሮ የሚንቀሳቀሰው፡፡ ፍ/ቤቶች ነፃ ተቋማት ናቸው እያለ፣ በአደባባይ የገዥው ፓርቲ መጠቀሚያ የሚያደርገው፡፡ ለዚህ ነው፣ ምርጫ ቦርድንም ጨምሮ ፣ሌሎችም ገለልተኛ ሆኖ ዜጐችን በእኩልነት ማስተናገድ ያለባቸዉ የመንግሥት ተቋማት ሁሉ የአንድ ገዥ የፓርቲ ጉዳይ አስፈጻሚዎች እንዲሆኑ የተደረገው፡፡

ከሁሉም በላይ ማስታወስ ያለብን ፣ እስካሁን ካለው ዓለም አቀፋዊ የዲሞክራሲ ተሞክሮዎች የኢሕአዴግን "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" የተለየና አስቸጋሪ የሚያደርገው፣ ከሁለቱም ዓለም የተገኘ ዲቃላ ፍልስፍና መሆኑ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም የሁለቱንም ዓለም በጎ ተግባራት የራቁት የፖለቲካ ስርዓትን ፈጥሮዋል፡፡ ለምሳሌ፣ የሶሻሊስት ዓለም የሚታወቀው የስራ ዋስትናን ለመስጠት በመጣሩ ነው፡፡ እነ ቻይና ወደ 1/5 የሚጠጋ የዓለም ሕዝብን መግበው የሚያኖሩት የሶሻሊዝምን በጎ ገጽታ በመጠቀም ነው፡፡ የኢሕአዴግ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" ተግባሩ ደግሞ ዜጎችን የስራ ዋስትና የሚያሳጣ መሆኑ ዛሬ የአደባባይ ሚስጢር ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ የካፒታሊስቱ ዓለም ከሞላ ጎደል የመደብለ-ፓርቲ የፖለቲካ ስርዓትን ስራ ላይ በማዋል፣ የፖለቲካ ዴሞክራሲን ለማስፈን ችሎዋል፡፡ በዚህም፣ ለዜጎች የመናገር፣ የመደራጀት፣ የመምረጥና የመመረጥ መብቶች ወዘተ አጎናጽፏል፡፡ ለዚህ ነው ፣በአንድ ትውልድ ውስጥ የአሜሪካው የሲቪል መብቶች እንቅስቃሴ በአሜሪካ የነበረው የዘረኝነት አስተሳሰብን ሰብሮ ኦባማን ለነጩ ቤተመንግስት ያበቃው፡፡ የኢሕአዴጉ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" ግን ላለፉት አርባ አመታት በኢትዮጵያችን በተደረገው የመብት ትግል በፈሰሰው በመቶ ሺዎች ደም ላይ የፈላጭ ቆራጭ አምባገነናዊ ስርዓት እንዲገነባ የሚያደርገው፡፡

አንዱ አስገራሚ የሆነው የኢሕአዴግ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" ስራ ለኢሕአዴግ ዴሞክራሲ ምሰሶ ሊሆን የሚችል አዲስ መካከለኛ መደብ (Middle Class) እየፈጠርኩ ብሎ መደሰኩሩ ነው:: የአዲስ መደብ ፈጠራውም በዋናነት በገሃድ የሚታይ፣ የኢሕአዴግ መሪዎችም እያዩትም፣ እየተሳተፉበትም ነው ለማለት ይቻላል፣ ሙስና እያደገና እያበበ እየሄደ ያለው:: ይህ የሚሆነው ደግሞ ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጧዋትና ማታ ሙስናን ለመጥፋት በመንግስት ዜና አውታሮች እየሰበከ በሚገኝበት ሰዓት ነው::

ይህ የኢሕአዴግ ዴሞክራሲ አስቸጋሪ ጠባዮች ሶሻሊስት ነው፣ የሶሻሊስት ስርዓት-ሕጎችን ይከተላል ሲሉት፣ «የነጭ ካፒታሊዝም» ፊቱን ብቅ ያደርጋል:: ካፒታሊዝም ነው ብሎ ሲጠጉት ፣የሶሻሊስት ገጽታውን ያወጣል:: ውጤቱም እላይ ማስቀመጥ እነደሞከርነው የሁለቱንም ዓለም ያልሆነና በሙስና የተዘፈቀ የካድሬዎች አስተዳደር መሆንና፣ ዴሞክራሲንም ሆነ ልማትን መምጣት ያልተሳካለት ስርዓት መሆኑ ነው:: በማያሻማ ቋንቋ ለማስቀመጥ፣ በኢትዮጵያችን የነገሰው ሁሉን አቀፍ ቀውስ ምንጩ በኢህአዴግ፣ ለኢህአዴግ ቁመት የተሰፋው ዴሞክራሲ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል::

ኢህአዴግ "በአብዮታዊ ዴሞክራሲው" አስተሳሰብ እድገት ይግለጽ እንጂ ከግንቦቱ ምርጫ ድንጋጤ ሲያገግም የራሱን ስራ ቁልጭ አድርጎ ባሳየበት ጽሁፍ የሚከተለውን ያትታል::

> የደርግን አምባገነን መንግስት ለመገርሰስ በወቅቱ በአገራችን ተራማጅ ኃይሎች ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ በነበረው የግራ ርዕዮተ-ዓለም በመመራት የተደራጁ የተለያዩ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ኃይሎች በሂደት የጋራ ግንባር ፈጥረው የደርግን አምባገነን አገዛዝ ገርስሰው በዋናነት በአርሶ አደሩ ላይ ተመስርተው አገሪቱን ከተቆጣጠሩ በኋላ ያለው የአገራችን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጉዞ ከኢህአዴግ ጉዞና ከኢህአዴግ አስተሳሰብ እድገት ጋር አብሮ የተያያዘ ነው:: (ኢህአዴግ፣ **1999** ገጽ **65**)

ይህ የኢህአዴግ ኑዛዜ የሚያሳየው አመጣጣቸው በግራው ዓለም «የአዲሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮት» ጋር የተቆራኘ መሆኑን ነው:: አከራካሪው ጉዳይ ግን "የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ" አስተሳሰብ ኢህአዴግ እንደሚለው እድገት አሳይቶ የመጻብለ-ፓርቲ ዴሞክራሲ ላይ የመድረሱ ጉዳይ ነው:: ከሁሉም በላይ ደግሞ የኢሕአዴግ መሪዎች እንደሃይማኖት ትምህርት የሚደግሙልን የብሔረሰቦች እኩልነት ተከብሮዋል ወይ ነው? ይበልጥ አጠያያቂው ጉዳይ ደግሞ እውን ኢህአዴግ እየገነባ ያለው ልማታዊ መንግስት ነው? የሚለው ጥያቄ ነው::

እዚህ ላይ መገንዘብ የሚያስገልገው ቁም ነገር ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ሆኖ የጻፈውን አብዱራህማን በቡ የሚባል ታንዛንያዊ ምሁር አባባል ለማዋስ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የፖለቲካ ስርዓት ከሌላ ዘር ከሆነ አባትና ከሌላ ዘር ከሆነች እናት የተገኘ/የተገኘች የበቅሎ ስርዓት ሆኖ ፣ ወይ የአባት ዘር ፣ ወይ የእናት ዘር የማይመስል ፣ ተወልዶ የማይበዛ ሥርዓት ነው :: ጧዋትና ማታ እንደሃይማኖት ትምህርት ቢደገምልንም የኢህአዴጉ የዲቃላ ስርዓት የሚባለውን ልማት እያመጣ

እንዳልሆነ ከማንም በላይ ዳቦ ያጣው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምስክር ነው፡፡ የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ልማትና ብልፅግና ፣ ላም አለኝ በሰማይ፣ ወተቷን የማላይ የሆነባቸው ሚሊዮኖች እንዳሉ ኢህአዴግም ያውቃል፡፡ ይህ መሆኑን ኢህአዴግም ስለሚያውቅ ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ ተስፋ ያልቆረጡትን ኢትዮጵያውያንን ዳግም ለማጭበርበር በእነታይዋንና ደቡብ ኮሪያ የተሳካ ልማት ያመጣውን የልማታዊ መንግስት ሞዴል በኢትዮጵያ ለመተግበር እየተንቀሳቀስኩኝ ነው የሚለው፡፡

የዓለማችንን ሁኔታ የሚከታተለው ማንም ሰው እንደሚያውቀው፣ ታይዋንም ሆነ ደቡብ ኮሪያ ዓለም በሁለት ጎራ በተከፈለበት የቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን የሶሻሊስቱም የካፒታሊስቱም ጎራ የሞትና የሽረት ትግል ያካሄዱበት ፣ ቀይ መስመሮች የተሰማሩባቸው ሀገሮች ናቸው፡፡ ሁለቱም ጎራዎች እልህ አስጨራሽ ውድድሮች ያካሄዱባቸው አካባቢዎች በመሆናቸው ታይዋንና ደቡብ ኮሪያ ብቻ ሳይሆኑ ተወዳዳሪዎቻቸው የነበሩት ቻይናና ሰሜን ኮሪያ ፣ በተለይም ቻይና የዓለም ኃያል መንግስታት ተርታ ገብታለች፡፡ ሰሜን ኮሪያም ብትሆን በተፈጥሮ ምክንያት የምግብ ምርት ችግር ቢኖርባትም፣ ጃፓንና አሜሪካንን የሚያክሉ ኃያላንን የምታስፈራ የኑክሌር ኃይል ሆናለች፡፡

በአንድ ፓርቲ አመራር ስር ሆኖ ውጤት በማምጣታቸው ብቻ እዛ የነበረው የቀዝቃዛ ጦርነት ዘመን ልዩ ሁኔታን ግምት ውስጥ ሳያስገቡ የነሱ ሞዴል ፎቶ ኮፒ እናደርጋለን ማለቱ ሲያንስ ከንቱ ልፋት ፣ ሲበዛ ከማጭበርበር ያለፈ ፋይዳ ያለው አይመስለኝም፡፡ በነገራችን "አብዮታዊ ዴሞክራሲው" የመጣው ከታይዋን ሳይሆን ከቻይና መሆኑንና ኢህአዴግ እየነገደ ያለውም ከታይዋን ጋር ሳይሆን ከቻይና ጋር መሆኑን መርሳት የለብንም፡፡

ሌላው ከግንቦቱ ምርጫ በኂላ የኢህአዴግ "የአብዮታዊ ዴሞክራሲ" መሐንዲሶች በኃይል ሳይገነዘቡት ወይም አውቆም ለመሳሳት የራሷን ምስል መስታወት ውስጥ እያየች የሌላ አራዊት ምስል መስሎዋት እንደምትገረም ጅንጀሮ ያስመሰላቸውን እውነታ "ልማት ዴሞክራሲና አብዮታዊ ዴሞክራሲ" በተባለው ጽሑፉቸው አስቀምጧል፡፡ ይህም እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

> የኪራይ ሰብሳቢነት ፓለቲካዊ ኢኮኖሚ የበላይነት ባገኘበት አገር የመንግሥትን ሥልጣን መቆጣጠር ከሞላ ጐደል ብቸኛው የመበልፀጊያ መሣሪያ ይሆናል፡፡ ሥልጣኑን የያዘና ሥልጣኑን ከያዘው ጋር በቅርብ የተሳሰረው ሁሉ ኪራይ መሰብሰቡን በሰፊው በማስኬድ እንደሚከብርና መንግሥት ሁሉንም እንደ ልማት አስተዋጽኦ እኩል ማስተናገድ ሳይሆን እንደ ቅርበቱ የኪራይ መሰብሰብ ዕድል እንደሚከፍትለት ስለሚታወቅ ሥልጣን መቆጣጠር የሞትና የሽረት ጉዳይ ይሆናል፡፡ ሥልጣን ለመያዝ የሚደረገው ሙከራ ሰላማዊ ወይ የአመፅና የጉልበት ፣ በዴሞክራሲ ሽፋን ወይም በግላጭ ፀረ-ዴሞክራሲ የሚካሄድ ሊሆን ይችላል፡፡ ዓላማው ግን አንድና ያው ነው ፣ ጥሎ ማለፍ ፖለቲካ ግዳይ ጥሎ ማለፍና ረግጦ የማሸነፍ (Zero Sum – game) ስለሚሆን ዘላቂነት ያለው ዴሞክራሲ ሊኖር አይችልም፡፡

በመቀጠል የኢህአዴጉ ሰፊ ጽሑፍ እንዲህ ይላል፣

> ዴሞክራሲ የምርጫ ውጤትን በፀጋ መቀበል የግድ ይላል:: ምርጫ የኪራይ ሰብሳቢነት ጥሎ ማለፍ በሚሆንበት ወቅት አሸናፊውና ተሸናፊው ኪራዩን የሚገሩበት የጋራ አቋምና ስምምነት ከሌለ በስተቀር ተሸናፊው ከኪራይ ሰብሳቢነት መረጣ የሚያስወጣው ውጤት በፀጋ የሚቀበልበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም:: /ኢህአዴግ 1999 ፣ ገጽ 83/

ኢህአዴግ ፣ ሌሎችን ቢከስበትም የራሱ ተግባር በትክክል የሚያስቀምጠውን ጽሑፉን ሲተነትን፣

> ኪራይ ሰብሳቢነት የበላይ በሆነበት ሁኔታ የፓለቲካ ትግሉ የአመለካከት ሳይሆን በዋናነት የኪራይ መሰብሰብ እድሎችን በሞኖፖል በመያዝ ወይም በመጋራት ጥያቄዎች ዙሪያ የሚከናወን ነው:: የሰለጠነና የተረጋጋ ትግልና የሥልጣን ሽግግር ሳይሆን የኑሮ መሠረትን በመገንባትና በመከላከል ዙሪያ የሚከናወን ፍልሚያ የሚካሄድበት ዴሞክራሲ ይሆናል::
>
> ኪራይ ሰብሳቢነት የዴሞክራሲ ፀር የሚሆነው መሪዎች የኪራይ ሰብሳቢነት አጀንዳቸውን .ለማሳካት ስለሚጠቀሙበት ብቻ አይደለም:: በዚህ ሁኔታ ሕዝቡ ከኪራይ ተጠቃሚ ባይሆንም ከፓለቲካዊ ኢኮኖሚ ተፅዕኖ ውጭ ሊሆን ስለማይችልና ይህም ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ ነው:: የኪራይ ሰብሳቢነት ፓለቲካዊ ኢኮኖሚ ሲሰፍን ሕዝቡ በራሱ ጥረት ሰርቶ ኑሮውን ለማሻሻል የሚያስችል የተሟላ ዕድልና ድጋፍ በእኩልነት አያገኝም ፣ ለልማት ባደረገው አስተዋጽኦ መጠንም ተጠቃሚ አይሆንም:: ለመንግሥት ሥልጣንና ለዋና ኪራይ ሰብሳቢዎች ባለ ቀረቤታ መጠን ቢያንስ ፍርፋሪ ማግኘት እንደሚቻል በተግባር ስለሚያይ ፍርፋሪውን ለማግኘት መሞከሩ የግድ ነው:: ስለሆነም በአካባቢ ፣ በሃይማኖት ፣ በብሔር ወዘተ ላንተ የቀረብን ነን የሚሉትና ኪራይ ከመሰብሰቡ ተግባር እንደሚያገሩት ቃል የሚገቡለትን የመከተል አዝማሚያ ይኖረዋል:: ፍልሚያው በኢኮኖሚ ወይም የፓለቲካ አቋም በሚያሳቸው ኃይሎች መካከል ሳይሆን ከላይ እስከታች በተዘረጋ የኪራይ ሰብሳቢነት መረቦች (Patronage Network) መካከል የሚከናወን ይሆናል::

ይህን ጽሑፍ በሰፊው የጠቀስነው ያለ ምክንያት አይደለም:: ኢህአዴግ የራሱን ሥራ ቁልጭ አድርጐ ያሳየበት ጽሑፍ በመሆኑ ነው:: ኢህአዴግ የደረደራቸውን ሥራዎች በገሃዱ ዓለም ማን በርግጥም እንደሚያደርግ የኢትዮጵያ ሕዝብ በየቀኑ ስለሚያይ ልዩ ምርመራ የሚያስፈልገው አይመስለንም:: የኢህአዴግ ሥራ ራሱም ይናገራል::

**ማጠቃለያ**

የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በሚባለው ፍልስፍና ከሁለቱም ዓለም የተለየ ዲቃላ ሥርዓት በመፍጠሩ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታም ሆነ ለልማትና ብልፅግና የማይመች አስቸጋሪ ሥርዓት ፈጥሮዋል:: ዋና ዋና ውጤቶቹም የሚከተሉት ናቸው::

1ኛ. እንደሚሰበከው በየትኛው ሚዛን ቢለካ ፣ እየተፈጠረ ያለው የመድበለ-ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት (Multi-party Democracy) ሰይሆን በተግባር (De Facto) የአንድ ፓርቲ መንግሥት ነው::

2ኛ. ፓርቲና መንግሥት በመጣመራቸው (Fusion of Party & State) ለዘመናዊ የውክልና ዴሞክራሲ (Representative Democracy) መኖር ወሳኝ የሆኑ የሥልጣን ክፍፍል (Separation of Powers) እና አንዱ የሌላውን ሥልጣን የመቆጣጠር ስልቶች (Checks and Balance of Power) በኢህአዴግ ዴሞክራሲ ሊፈጠሩ አልቻሉም:: ይህም ያለውን ሥርዓት በዴሞክራሲ ጐራ ሳይሆን በአምባገነናዊ ሥርዓቶች ጐራ እንዲመደብ አድርጐታል::

3ኛ. የሥልጣን ክፍፍል ባለመኖሩም ሕግ አውጭ የሆነው ፓርላማውና ፣ ሕግ ተርጓሚ የሆኑት ፍ/ቤቶች ሙሉ በሙሉ ሥራ በአስፈጻሚው ተፅዕኖ ሥር እንዲወድቁ ተደርጐዋል::

4ኛ. የሥራ አስፈጻሚው ያልተገደበ ሥልጣንም የሰብአዊ መብቶች ጠባቂ ኮሚሽን ፣ የእንባ ጠባቂ መሥሪያ ቤት ፣ የምርጫ ቦርድ የመሳሰሉት ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ጉልህ ሚና የሚጫወቱ ተቋማት ደካማ ብቻ ሳይሆኑ ከሥራ አስፈጻሚው ጉዳይ ማስፈፀሚያነት እንዳያልፉ ሆነዋል:: እዚህ ላይ በተለይ ልብ ማድረግ የሚያስፈልገው ጉዳይ ኢህአዴግ "ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ " እምነቱ በመነሳት መንግሥትን የገዥው ፓርቲ (መደብ) የመጫቆኛ መሣሪያ አድርጐ መመልከቱና በተግባር ለማዋልም መንቀሳቀሱ ነው::

5ኛ. የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የእውነተኛ ዴሞክራሲ ተፃራሪ በመሆኑ ነፃ ሚዲያና ነፃ የሲቪል ማህበር ድርጅቶች እንዳያብቡ ታፍነዋል::

6ኛ. ዴሞክራሲ በዳበረባቸው ሀገሮች ከፓለቲካ ፓርቲዎች ውድድር ገለልተኛ ሆኖ መገልገል ያለባቸው እንደ ሲቪል ሰርቪስ ፣ ፖሊስ ፣ የሀገር መከላከያ አባላት ወዘተ በኢትዮጵያችን የአንድ ፓርቲ ጥቅም አስከባሪዎች ሆነዋል::

7ኛ. ያለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውነተኛ የሆነ የፌዴራል ሥርዓት መኖር ስለማይታሰብ፣ ብዙ የተባለለትና የብሔረሰቦችን እኩልነት አምጥተዋል ተብሎ እየተነገረለት ያለው የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ዴሞክራሲ አልባና የገዥው ፓርቲ የከፋፍለህ ግዛ ሴራ መጠቀሚያ ከመሆን ሊያልፍ አልቻለም:: እንደውም ፣ታላቋን ሶቪየት ህብረትንና ዩጐዝላቪያን ያፈረሰው

ዴሞክራሲ አልባ የይስሙላ ፌደራሊዝም ስለሆነ ፣ በኢትዮጵያችንም ሊመጣ የሚችለው አደጋ ሊታሰብበት ይገባል::

8ኛ. በችግሮች በተተበተበው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፍልስፍና ምክንያት ፣ መንግሥት ለሁሉም ዜጐች የሚጠቅም ፣ ግልጽና አሳማኝ የሆነ የኢኮኖሚ ፓሊሲ ማውጣትና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መፍጠር ባለመቻሉ ብዙሃኑ ለአስከፊ ድህነት የሚዳረጉበት፣ ጥቂቶች ያለልፋት የሚከብሩበት ፣ በሙስና የተዘፈቀ ሥርዓት ከመፍጠሩም በላይ ለልማትና ብልፅግና የመሠረት ድንጋይ ይሆናል የሚባለው የገበያው ሥርዓትም በአንድ በኩል በገዥው ፓርቲ የንግድ ተቋማት የውድድር ሜዳው ሲዛባበት ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በዋጋ ግብሸትና ኢኮኖሚ ቀውስ የሚነጥ ሜዳ ሆኖዋል::

9ኛ. የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የፍልስፍና መሠረቱ የአንድ ፓርቲ አምባገነናዊ ሥርዓት መፍጠር እንጂ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ብሔራዊ መግባባት መፍጠር ስላልሆነ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለማፈንና ለማጥፋት የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የሀገሪቷን ፓለቲካ በግጭቶችና ፍጭቶች እንዲሞሉ አድርገዋል::

10ኛ. በመጨረሻም የኢህአዴጉ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" ከሁሉም በላይ መንግሥት የአንድ ፓርቲ የግል ሀብት የሚያደርግና የመንግሥት ተቋማት ዋና ሥራቸው መሪዎችን ሥልጣን ላይ ለማቆየት የሚንቀሳቀሱ በፈረንጂኛ Shadow State በሕግ የሚታወቀው መንግሥትን ተክቶ የሚሠራ መፈጠሩ ነው:: የዚህ ሁሉ ችግሮች እናት (Mother of all Problems) ደግሞ ከኢህአዴጉ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" የሚመነጨው የአንድ ፓርቲ የበላይነት (Hegemony) ሕልም ነው::

## <u>መደምደሚያ</u>

ለኢህአዴግ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" አማራጩ የግድ ያሉትን ችግሮች የሚፈታና የተሳኩ ዓለም አቀፍ የዴሞክራሲ ተሞክሮዎችን ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል:: ይህ ማለት፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ዋናው ጉዳይ "አብዮታዊ ዴሞክራሲን" መመሪያው ያደረገ የአንድ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭ የሆነውን አገዛዝን አውርዶ የመድብለ-ፓርቲ ዴሞክራሲን በማስፈን የሕዝብ ተጠያቂነት የተቀበለና በሕግ የበላይነት የሚያምን መንግስትን ማቋቋም ነው::

ይህ የሚሆነው ደግሞ የዴሞክራሲ አወላጅና መተግበሪያ ትልቁ መሳሪያ በሆነው ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመፍጠር የዴሞክራሲ ተቋማት እንዲያብቡ ማስቻል ነው:: በዓለም ላይ ያሉ የዴሞክራሲ ስርዓት ተሞክሮዎችና ሞዴሎች ከዚሁ ከነፃና ፍትሐዊ ምርጫ የተወለዱና ያደጉ ናቸው::

በኢትዮጵያችን እንዲመጣ የምንመኘው ዴሞክራሲያዊ ሞዴል ወይም ስርዓት የሚከተሉትን የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል::

1ኛ: የመድብለ-ፓርቲን ዴሞክራሲን ለይስሙላ ሳይሆን ፣ በተግባር የተቀበለ መንግስት፣

2ኛ: ዋናው ስራ አስፈጻሚና የሕግ አውጭው ክፍል በነፃና ፍትሐዊ ምርጫ የተመረጡ መሆናቸው የሚያረጋግጥ ፓለቲካ ሥርዓት ፣

3ኛ: የሕግ በላይነት መኖሩን የሚቆጣጠርና ነፃ ፍ/ቤት እንዲሰየም የሚያደርግ ፣ ሁሉም ዜጋ በሕግ ፊት እኩል መሆኑን የሚያረጋግጥ ፣

4ኛ: የዴሞክራሲ ተቋማት ነፃና ገለልተኛ ምርጫ ቦርድ ነፃ ሚዲያና ነፃ የሲቪል ማኅበረሰብ መኖር በተግባር የሚቀበል መንግሥት ፣

5ኛ. በዴሞክራሲ ላይ የተመሠረተ እውነተኛ የፌዴራል አስተዳደርን የሚያሰፍን የፓለቲካ ሥርዓት ፣

6ኛ. በሕዝብ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የሚፈጥር የፓለቲካ ሥርዓት ፣ በመጨረሻም የዜጎች ይሁንታ (Mandate of Heaven) ያለውና የሚፈጥራቸው ተቋማት አገልግሎታቸውም ሆነ ተጠያቂነታቸው ለሕዝብ ወይም በሕዝብ የሆነ መንግሥት መፍጠር ናቸው:: እንዲህ ዓይነቱ የፓለቲካ ሥርዓት ከሞላ ጐደል በቀኝ ዘመም የፓለቲካ ኃይሎች ሊመሠረት ከሚችል ሊብራል ዴሞከራሲ እስከ በግራ ዘመሞች ሊመሠረት እስከሚችል ሶሻል ዴሞክራሲ የሚያጠቃልል ነው::

**References**


Bratton, M. and van de Walle (1993) 'Neopatrimonial Regimes and Political Transitions in Africa', Working Paper No. 1, MSU Working Papers on Political Reform in Africa, East Lansing.

Bratton, M. & N. v. de Walle (1997) *Democratic Experiments in Africa: Regime Transformation in Comparative Perspective.* Cambridge: Cambridge University Press.

Dahl, R. A. (1976) *Modern Political Analysis* (Third edition). Englewood Cliffs, N.J.: Prentice-Hall, Inc., Englewood Cliffs House.

Diamond, L. (ed.) (1992) *Democratic Revolution: Struggles for Freedom and Pluralism in the Developing World*, *Perspectives on Freedom*, No. 12 (Freedom House)

EPRDF (2006) *Yeabiyotawi Demokrasi Estrategi, Taktikina Yeamarar Tiyake* (in Amharic), Addis Ababa.

EPRDF (2006) *Limat, Demokrasina abiyotawi Demokraci* (in Amharic), Addis Ababa.

Huber, E. D. Rueschemeyer, and John D. Stephens (1997) 'The Paradoxes of Contemporary Democracy', *Comparative Politics* Vol. 29 No. 3 (1997): 323 - 342.

Lipset (quoted in Vanhanen 1997)

Pennock (quoted in Vanhanen 1997)

Schedler, Andreas (ed.) (2006) *Electoral Authoritarianism: The Dynamics of Unfree Competition*. Boulder & London: Lynne Reinner Publishers.

Vanhanen, T. (1997) *Prospects of Democracy: A Study of 172 Countries*. London and New York: Routledge.


www.ethiomedia.com